# የአሥመራው “ነውጤ” ምን እያሉ ይሆን?

**አዲሱ ለማ - ከሰሜን ማዘጋጃ**

ሀሎ ... ሀሎ አሥመራ! ከወደ አሥመራ ምን ይወራል? ምን ይሰማል? ምን ይነገራል? መቼም ግጥምና ዜማው ባልተለወጠበትና አቀንቃኙም ያው በምናውቃቸው ሰውዬ ሁሉም የሚከወንበት በመሆኑ ቢሰለቻችሁ አይገርምም፤ አይፈረድባችሁምም። ከትናንት ወዲያ፣ ትናንት፣ ዛሬም ጨዋታው አልተቀየረላችሁም። ዘወትር ጭንቀት፣ ግጭት፣ ወረራ፣ ስደት፣ ጦርነት። ሁሌም ሕይወት በስጋት። ታድያ ሰሞኑንም ይኸው መነሻውን ከወደ አሥመራ ያደረገው አውሎ ንፋስ ይዞት የመጣው ወሬ አዲስ ባይሆንም የተለመደ ነው ብዬ ላልፈው ግን አልፈቀድሁም።

የአሥመራው ቤተመንግስት ሰውዬ ከውስጥ የተቀሰቀሰባቸውን ሕዝባዊ አመፅና ቁጣ ለማርገብ ዛሬም ያንኑ ያልተቀየረ የተለመደ ግጥማቸውን አሰነዳድተው በዚያው በተሰለቸው ዜማቸው ታጅበው ማላዘንን ይዘዋል። ደግነቱ ለዚህ የቅጥፈት ድርሳናቸው ጆሮ የሚያውሳቸው ያገኙ አይመስልም።

ሰውዬው የሕዝባቸው ኑሮ አልለወጥ፣ አልሻሻል ሲላቸው፤ የአገር ቤቱ ውስጣዊ ቀውስ ሲበረታባቸው የችግሩ ማብረጃ ስትራቴጂ የትኩረት አቅጣጫ ማስቀየሪያ ስልቱ የማተረማመስ አጀንዳቸውን ገላልጠው፤ ማነው ባለሣምንትን አፈላልገው በነገር መተነኳኮስን ነው። ለዚህም ሲሉ የማይፈነቅሉት ድንጋይ አይኖርም።

የአሥመራው ሰውዬ ከመረጋጋት፣ ከሠላምና ከወዳጅነት ጋር ያላቸው የጠላትነት መንፈስ አሁንም አልቀዘቀዘም። በዚያን ሰሞን ሰውዬው - “ጭር ሲል አይወዱም” በሚል ርዕስ አንድ ፀሐፊ ዋቢዎችን ጠቃቅሰው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ለህትመት ያበቁትን ስለማንበቤ አስታውሳለሁ።

ፀሐፊው እውነት አላቸው። የአሥመራው ነውጤ ራሳቸው ታውከው የሌላውን ሠላም ለማደፍረስ የማይተኙ፤ እንደ አበደ ውሻ ተቅበጥብጠው ይህንንም ያንንም ከመልከፍ እንደማይቦዝኑ ከተረዳሁ ሰነባብቻለሁ። የመንና ሱዳንን ልብ ይሏል? ኢትዮጵያና ጅቡቲንስ ያስታውሷል?

አሁን ከሰሞኑ ደግሞ እኚሁ ነውጤ የ“ገና ስጦታ” መሆኑ ነው መሰል ከአሥመራው ቤተመንግሥታቸው ሆነው “የኢትዮጵያ ሠራዊት በዛላንበሳ ግንባር ጥቃት ፈፅሞብኛል” የሚል የቅዥት ነጠላ ዜማቸውን ለቀዋል። ምን ለማትረፍ ምን ለማግኘት እንደሆነ ወደ ኋላ ላይ የምናየው ይሆናል። መሬት ላይ ያለው ሀቅ ግና ከነውጤው የቅጥፈት ወሬ እጅጉን የራቀ የመሆኑ ጉዳይ ይበልጡን ሰውዬውን ትዝብት ላይ ጥሏቸዋል።

በግልፅ እንደሚታወቀው በኢትዮጵያና ኤርትራ ድንበር አሁን ያለው እውነታ ከወትሮው ማለትም ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ ከነበረው የተለየ አይደለም። ፈረንጆቱ “NO PEACE, NO WAR“ /ሠላምም ጦርነትም የለም/ ከሚሉት ደረጃ ላይ ነው የሚገኘው።

የኢትዮ - ኤርትራ የድንበር ጥያቄ በሠላማዊ መንገድ ብቻ የመፍታቱ አማራጭ በኢትዮጵያ በኩል አሁንም ቢሆን በማያሻማ መልኩ ተቀባይነት ያለው ጉዳይ መሆኑ እንዳለ ሆኖ።

ይህን ጉዳይ አስመልክቶ የኢትዮጵያ መንግሥት በተደጋጋሚ ጊዜ አቋሙን ፈፅሞውኑ በማያሻማ መልኩ ይፋ አድርጓል። ወደ ጦርነት የመግባት አማራጭን እንደማይመርጥም ፍላጐቱን በግልፅ አሳውቋል።

በዚህ በዛሬው በሰለጠነው ዓለም ውስጥ የሚከሰቱ ልዩነቶች፣ ውዝግቦችና አለመግባባቶች በሠላማዊ መንገድ የመፍታቱ ሂደት ቁጥር አንድ ተመራጭ የመሆኑና ሚዛን የመድፋቱ ጉዳይ አጠያያቂ አይደለም። ለዚህም ሲባል ነው የኢትዮጵያ መንግሥት ለድንበር ውዝግቡ መፈታት ሠላማዊ አማራጭን ሊተካው የሚችል አንዳች ነገር የለም እያለ ደጋግሞ የሚሰብከው። ዳሩ ምን ያደርጋል የአሥመራው ነውጤ ጥያቄና ፍላጐት ከመሬት ጉዳይ ጋር ብቻ የተያያዘ ባለመሆኑ መጨበጫና ውሉ ጠፍቶባቸው አንዱን ያነሳሉ፣ ሌላውን ይጥላሉ፣ ለያዥ ገላጋይም አስቸጋሪ ሲሆኑ ይታያሉ።

በሁለቱ አገራት ድንበር አካባቢ ያለው ወቅታዊ እውነታ "ሠላም የለም፤ ጦርነትም የለም" ሁለተኛው አማራጭ ከሙሉ ጦርነት የተሻለ ስለሆነ ብቻ በኢትዮጵያ በኩል ተመራጭ ሆኖ ተይዟል። ከጦርነት መልካም ነገር ስለማይገኝ በምንም ዓይነት ሁኔታ ጦርነት ለመፍትሄው ተቀዳሚ ተመራጭ ሆኖ በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል አይወሰድም።

እንደ አሥመራው ሰውዬ ፍላጐት ቢሆን ኖሮማ ለድንበር ጥያቄው መቋጫ ሌላ ... ሌላ አማራጮችን ሁሉ መያዝ በፈቀዱ ነበር። ዳሩ ምን ያደርጋል ! ፍላጐትና አቅም አልጣጣም ብሏቸው እንጂ።

ይህም ሆኖ ሰውዬው እጃቸውን አጣጥፈው አርፈው አልተቀመጡም። ይሆኑኛል፣ ያዋጡኛል የሚሏቸውን እድሎች ሁሉ ከመጠቀም ቦዝነው አያውቁም። "ባድመን ለቀን መውጣት ማለት ፀሐይ መጥለቋን አቆመች" ብለው በተሳለቁ ማግሥት በ"ዘመቻ ፀሐይ ግባት" የነበረው እንዳልነበር ሆነ። ይህም የቅርቡ ትዝታችን ነው። ሠራዊታቸው ቁምጣው ተገልቦ የኋሊት ከተገረፈበት ከዚያን ጊዜ አንስቶም ቢሆን ሰውዬው ያንቀላፉ ይመስሉ እንጂ ሙሉ በሙሉ አልተኙም።

በኪሣራ ፖለቲካ አራማጅነታቸው መላው ዓለም ጠንቅቆ ያወቃቸው የአሥመራው ነውጤ ፊት ለፊት ጦርነት ገጥመው ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ይጠፋቸዋል ማለት የዋህነት ነው። አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ይህን ይመርጧታል ተብሎ አይገመትም - ለይቶላቸው ካላበዱ በቀር።

ከዚህ ይልቅ የአሥመራው ነውጤ አኩራፊ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎችን በጉያቸው አሰባስበው ለጥፋት መሣሪያነት ማደራጀት፣ ማሰልጠን፣ ማስታጠቅና ለዚሁ ተግባር ወደ አገር ቤት አስርጐ በማስገባት ሽብር ለማንገስ ላይ ታች ማለት አሁን ... አሁን ይበልጡን የሚታወቁበት ተግባራቸው ሆኗል።

እኚሁ ነውጤ በግልፅ በአደባባይ 'ኤርትራ ለሌሎች ኃይላት የመሣሪያና የፖለቲካ ድጋፍ የመስጠት መብት አላት' ብለው ያለእፍረት የመናገራቸው ጉዳይ ምንን እንደሚያመላክት ልብ ይሏል?

የግንቦት 7ቱ አመራር አንዳርጋቸው ፅጌ የዚያን ሰሞን የአሥመራ ቆይታውና ከነውጤው ጋር ያደረጋቸው ምክክሮች፤ ራሱን የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ብሎ የሚጠራው ኦነግ ለማረፊያነትና ለስልጠና ማዕከልነት ኤርትራን በተመራጭነት መያዙ በቂ ከበቂም በላይ መልካም ማሣያ ነው።

ምን ይህ ብቻ! የአሥመራው ነውጤ በጥፋት የተሞሉ ረዥሹም እጆቻቸውን ድንበር አሻግረው በሶማሊያ በኩል የእጅ አዙር ጥቃት ፈፅመው በውጤቱ ምን እንደተከናነቡ ጠንቅቀው ያውቋታል።

ኤርትራ ውስጥ ዛሬ መጠነ ሰፊ ውስብስብ ችግሮች ከቁጥጥር ውጪ የመውጣታቸው ጉዳይ የአሥመራውን ነውጤ እረፍት ነስቷቸዋል። አንድ ... ሁለት ማሣያዎችን ልጠቃቅስ።

በቆላማውና ደጋማው የኤርትራ አካባቢዎች በሚኖሩ ዜጐች መካከል ልዩነት በመፈጠሩ የጥላቻ ስሜት ነግሷል።

የሻዕቢያ መንግስታዊ መዋቅር በጠንካራ መሠረት ላይ አለመቆሙ ባለሥልጣናቱ እርስ በርስ በጥርጣሬ ዓይን እንዲተያዩ ምክንያት እየሆነ መጥቷል።

ከአጠቃላዩ የኤርትራ ሕዝብ መካከል ሁለት ሦስተኛው የሚልስ የሚቀመሰው አጥቶ እለታዊ ኑሮው እጅጉን ፈታኝ ሆኖበታል።

እንግዲህ ይህ ሁኔታ እያለ ነው ኤርትራ ከአጠቃላይ አገራዊ ምርቷ ገቢ ውስጥ
6 ነጥብ 3 በመቶውን ያህል ለጦር መሣሪያ ሸመታ የምታውለው። በዚህ ስሌት ከአጠቃላይ አገራዊ ምርታቸው ገቢ አንፃር ለጦር መሣሪያ ግዥ ከፍተኛ ወጪ ያወጣሉ ተብለው ከተዘረዘሩት አሥር የዓለማችን አገሮች መካከል ኤርትራ በዘጠነኛ ደረጃ ላይ የምትገኝ ብቸኛዋ አፍሪካዊ አገር ሆናለች።

በስኮትሆልም አለም አቀፍ የሠላም ምርምር ተቋም ጥናታዊ ሪፓርት መሠረት ከአጠቃላዩ አገራዊ ምርታቸው ገቢ አንፃር ሲመዘን ለጦር መሣሪያ ከፍተኛ ወጪ ያወጣሉ ከሚባሉ የአፍሪካ አገራት ጐረቤታችን ኤርትራ ቀዳሚዋ ናት።

ድንቄም! "የምትበላው የላት የምትከናነበው አማራት" ይላል የአገሬ ሰው እንዲህ ዓይነት ሁኔታ አላምርህ ሲለው። የሣይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶችን፣ ለእርሻና ኢንዱስትሪ ምርቶች ማበልፀጊያነት የሚረዱ ዘመናዊ መሣሪያዎችን ወደ አገር ቤት በማስገባት ረገድ ይህች ምስኪን አገር ከቀዳሚዎቹ ጐራ ተፈርጃ ቢሆን እንዴት ሸጋ በሆነ - ወይ አለመታደል።

እኚህ ነውጤ የሚመሩት የሻዕቢያ መንግሥት በተለይ በአፍሪካ ቀንድ በሠላም አደፍራሽነቱ ከሚታወቅበት ግልፅ ባህሪው ባሻገር ለአክራሪና ለፅንፈኛ አሸባሪ ቡድኖች በኋላ ደጀንነት መቆሙ ከዓለም ሕዝብ የመገለል ፅዋን እየጐመዘዘውም ቢሆን እንዲያጣጥም ተገዷል። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት በቅርቡ በኤርትራ ላይ የጣለው ማዕቀብ የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ስለመሆኑ ሳይዘነጋ ማለት ነው።

ጽሑፌን ላጠቃልል። ለዓለም ዓቀፍ ህግና ሥርዓት ደንታ ቢስ በሚኮንበት፤ ዜጐች በሠላም ወጥተውና ገብተው ሰርቶ ለመኖር ዋስትና በማያገኙበት በዚያች አገር ነገር ዓለሙ የማይያዝ የማይጨበጥ እየሆነ መጥቷል።

የአሥመራው ነውጤም አንድ እግራቸውን ከመቃብር ሰደው እንዲህ ነው፤ እንዲያ ነው ይሉናል። በተራ ፕሮፖጋንዳቸው ሊያታልሉንና ሊቀጥፉን ይዳዳቸዋል። እባክዎን ውጥንቅጡ የወጣውን የቤት ሥራዎን በቅጡ ይወጡ - ምክሬ ቢሆን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሆነ ጠላቴ ብሎ በፈረጀው ድህነት ላይ የጋራ ክንዱን አስተባብሮ ከተነሳ ሰነበተ። ውጤቱንም መቋደስ ከጀመረ ቆየ።

በእብሪት በመወጠር ሠላማዊ አማራጮችን ለምኔ ብለው አራክሰው፤ ለሠላም ሲባል የተነጠፉ ሥጋጃዎችን ባልፀዱ እግሮች ረጋግጠው ጥለው፤ የተበረከቱ የሠላም አበባዎችን ቀጣጥፈው እንዲያጠወልጓቸው ዛሬ ማንም ፍቃድ አይሰጥዎትም።

አይነኬ፣ አይደፈሬ የተባሉት የሻዕቢያ ምሽጎች በምን ያህል ቀናት ውስጥ ዶግ አመድ ሆነው እርቃናቸውን እንደቀሩ ያስታውሳሉ? ከዘነጉ ላስታውስዎት።

በሠላማዊ መንገዶች በሮች ላይ የብረት በሮች ከተቸነከሩባቸው ሦስተኛውን አማራጭ መጋትዎ እንግዲህ አይቀሬ ይሆናል። ለዚህም የተሰጠውን ሕዝባዊ አደራ በፅናት ተረክቦ ከግብ ማድረስ የሚችል ጠንካራ የመከላከያ ኃይል እንዳለን የቅርቡም የሩቁም እንዲያውቀው ይመከራል። አበቃሁ - ቸር ይግጠመን።